# መገንባት እንደሚችል ያሳየ ለማፍረስ የሚተባበረው አያጣም –

ተፈራድንበሩ
July 5, 2016

አዎን ለ"ፍትሕ"፣ ዲሞክራሲ፣ "እኩልነት"፣ ወዘተ… በሚሉ የተስፋ ቃላት የሕዝቡን ብሶት ተጠቅሞና አታሎ በመመረሽ የአገሪቷን ርዕሰመስተዳድር/ቤተ-መንግሥት/ ከተቆጣጠረ በኋላ እነዚያን የሚጣፍጡ መፈክሮች ሁሉ የውሀ ሽታ አድርጎ ውንብድናውን በሥልት በሥልቱ እያስፋፋ ታይቶ በማይታወቅ የአገር ክህደት አገራችንንና ሕዝቦቻችንን ለውርደት የዳረገውን ሥርዓት ማፍረስ አስፈላጊ ነው፤ ነገር ግን አብሮ መታየት እና አብሮ መታቀድ ያለበት ኅብረቱ የሚያስፈልገው ለመገንባትም ነው። ብዙዎች የፖሊቲካ ድርጅቶች ከተቃወሚዎቻቸው ጋር በጠረጴዛ ዙሪያ ተነጋገረው በጋራ መስኮች አብረው መሥራታቸውን ለሕዝብ አላሳዩም። አንዳንዶቹ እንዲየውም ስለአገር ጉዳይ ከተቃዋሚዎቻቸው ጋር በጋራ መታገልን የሚፈሩት ይመስላል። ሌሎች ደግሞ በጋራ ለመሥራት መጀመራቸውን አብሥረውናል። እሰየው ቢያሰኝም "ዓይን አይቶና ጆሮ ሰምቶ ልብ ይፈርዳል" ይባላል። ሆኖም የተቃዋሚነት ስም ብቻ በመያዝ በተስፈኛነት መና ከሰማይ እስኪወርድ በምኞት የሚጠባበቁ ሥልጣን ናፋቂ ቡድኖችም አሉ፤ ያለተገቢ ሥራ በተስፋ የሚገኝ ምንም ነገር ስለሌለ ተጨባጭ ሥራ መሥራት የግድ ነው፤ የሎተሪ ዕድል እንኳ ለመመኘት ትኬት መግዛት ያስፈልጋል።

የወያኔ ሥርዓት ይፍረስ፤ ወያኔ ይወገድ፤ የሚሉ አስተሳሰቦች ብቻቸውን የአውራ ጎዳና መፈክሮች ሆነው ይቀራሉ፤ እነዚህን ከአፍ የማያልፉ መፈክሮችን ምእራባውያን አገሮች የተወሰነ ሰላማዊ ሕዝብ ስልፍ አድርጎ የአገር መሪዎችን ምስልና ሌሎች አርማዎችን ቢያቃጠል እንኳ ወደአመጽ እስካላደገ ድረስ ሆድ የባሳቸውን የሕዝብ ክፍሎች እንደ የስሜት ማስተንፈሻ መንገድ ይጠቀሙባቸዋል። ለስም ተቃዋሚ ወይም ለውጥ ይመጣል በሚል ምኞት ተስፋ ዘመናትን ሲቆጥር የሚኖርም ሆነ በአገር ተጨባጭ ሁኔታና በሕዝቦች ፍላጎት መመራት የማይችል ድርጅት ሕዝባዊ ግብ ላይ ሳይደርስ የወረቀት ላይ ነብር ሆኖ ይኖራል። ምክንያቱም ከሕዝቦች መሠረታዊ ፍላጎት ስለሚርቅ ነው። እንደዚህ ለስሙ ተቃዋሚ ሆኖ ሕዝቡን የተስፋ ዳቦ ከመመገብ ምንጭ በመቆፈር፣ ክሊኒክ በመሥራት፣ በኩበት ጭስ ዓይናቸውን የሚጎዱ እናቶችን መፍትሔ እንዲያገኙ በመርዳት፣ ወዘተ… የተጎዳውን ወገናቸውን ቢታደጉት ይሻል ነበር።

በተረጋጋ መንፈስና ሚዛናዊ ኅሊና ሲታይ ተራውና አብዛኛው ሕዝብ የመንግሥትን መፍረስ በጥንቃቄ ነው የሚመለከተው፤ ሙያዬ የሕዝብ አስተዳደር/Public Administration/ ስለነበር፤ ለመመረቂያ ጽሑፌ ከ 36 ዓመታት በፊት ከተጠቀምኩባቸው ቃለመጠቆች አንዱ "መንግሥት ባይኖር ምን ችግር አለው?" የሚል ነበር፤ ከ 180 የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ተጠያቂዎች መካከል 9 መልስ አልሰጡም፣ 40 መንግሥት የመጭቆኛ መሣሪያ ስለሆነ ባይኖር ምንም ጉዳት የለውም፤ 48 ለሕዝብ የቆመ ከሆነ ይኑር ሲሉ፤ 83 ደግሞ ማንኛውም ሕዝብ አካባቢውን ያስተዳድር ለጋራ መከላከያ፣ ለጋራ ገንዘብ፣ ለጋራ መገናኛ እና የጋራ ሀብቶችን አስተባብሮ ለማልማትና በጋራ በእኩል ለመጠቀም ከሁሉም አካባቢ ሕዝብ የተውጣጣ አስተባባሪ (ፌደራል መንግሥት) እንዲኖር ሐሳብ ሰጡ። ያው ጥያቄ ለፋብሪካ ሠራተኞች ታድሎ የሚከተለው ምላሽ ተገኝቷል፦
19 መልስ አልሰጡም፤ 21 መንግሥት የመጨቆኛ መሣሪያ ስለሆነ አያስፈልግም፤ 136 ለሕዝብ የቆመ ከሆነ መንግሥት ቢኖር ጥሩ ነው፤ 4 ሕዝብ አካባቢውን እያስተዳደረ ፌደራላዊ አመራር ይኑር አሉ።

ከምላሾቹ እንደሚታየው አብዛኞቹ የመንግሥትን መኖር የሚደግፉ ሲሆን በይዘቱና ዓይነቱ ላይ ግን ይለያያሉ። ይህ አገርን የሚወክል በቂ ጥናት ባይሆንም፣ የሕዝብ አስተሳሰብ በሚዛናዊ ምክንያቶች እንደሚለያይ የሚጠቁም ነበር።
ሕዝብ የሚያደርገውን ነገር ሁሉ እያስተዋለና እያመዛዘነ ስለሆነ የሚፈጽመው ባህር እንደሚገባ ዓሣ ዘሎ ዘው አይልም። ዘው ብሎ እንዲገባ የሚያደርገው አሳማኝ እና ተጨባጭ ሁኔታ መኖር አለበት ማለት ነው፤ ምክንያቱም በማናቸውም ችግር በግምባር ቀደምትነት የሚጎዳው ሰፊው ወይም ደሀው ሕዝብ ነውና። ሠርቶ መኖር፤ የዘራውን አምርቶ መሰብሰብ፤ በሰላም ወጥቶ በሰላም መግባት፣ ባለው ጥሪት ልጆቹን በማሳደግ ቤተሰቡን ማስተዳደር የሚፈልግ ቤተሰብ ሰላም የሚነሣው ሳይሆን በሰላም ተከባብሮ

የሚኖር ጎረቤት እንዲኖረው ለማድረግ የሚችልበት ነባራዊ ሁኔታዎች እንዲኖሩለት ይፈልጋል። ማንኛውም ቤተሰብ ጨቋኝ መንግሥት ባይፈልግም፣ የልጆቹና የቤተሰቡ ደህንነትም ትልቅ ጉዳዩ ነው፤ ጎረቤቱ ሲረበሽ፣ ሲያዝን ሲጨነቅ በደስታ የሚኖር የለም። ሌላው ቀርቶ በሚያምንበት የአገር አድን ዘመቻ የሚዘምት ሰው ወደጦር ሜዳ ሄዶ በጤና ስለመመለሱ እንኳ እርግጠኛ በልሆነበት ሁኔታ የልጆቹና ቤተሰቡ ደህንነት ጥያቄ ውስጥ እንዳይገባ ይፈልጋል። ነፃነት ያለትግል በቀና መንፈስ ወይም በችሮታ እንደማይገኝ በተደጋጋሚ ታሪክ ያሳየን ሲሆን፤ በአንፃሩ ትግል በባዶ ፉከራና ግብታዊ አሠራር ሳይሆን በዕቅድና በስትራተጂ መሆን ይኖርበታል ለማለት ነው።

ትግልም ድልም የሕዝብ ስለሆነ ሕዝብ በሚገባ ያልተሳተፈበት ትግል ለሕዝባዊ ድል መብቃቱ አጠራጣሪ ነው። ሕዝብ ስንል ማንኛውንም ሕጋዊ ሰውነት ያለውን ሰው – በዋና ከተሞች ውስጥ የሚገኘውን ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ለከብቱ የግጦሽ ሣር በማጣት፣ በዘርና ማዳበሪያ አቅርቦት፣ በዝናብ እጥረት ምክንያት ቡቃያው ሜዳ ላይ የሚደርቅበትን፣ ኑሮውን ለማሸነፍ ቆላ ደጋ እየናወጠ ቸርችር አዳረውን፤ በኑሮ ውድነትና በተለያዩ በሽታዎች የሚሰቃየውን፣ ከኑሮው ተፈናቅሎ በገዛ አገሩ ስደተኛ የሆነውንና የወገን ያለህ የሚለውን፣ ሥራ አጡን ጭምር ነው። ሕዝብ የሚባለው ወንድ፣ ሴት፣ ሕፃን፣ ሽማግሌ፣ ብሎ በዘር፣ ቀለም፣ እምነት፣ ቋንቋ፣ ባላገር፣ ከተሜ፣ ወዘተ… ሳይለይ መሆኑ ቢታወቅም፣ ብዙ የፖሊቲካ ድርጅቶች ሕዝብ የሚለውን ቃል በተግባር ለምሳሌ ሕዝቡ ይደግፈናል ብለው የሚገልጹት እነሱን የሚያቃቸውንና የሚደግፋቸውን የሕዝብ ክፍል ብቻ ነው። የቀረውን ሕዝብ እነሱም ስላልተቀላቀሉት በውስጡ ተንቀሳቅሰው ወይም ለችግሩ መፍትሔ ጠቋሚ ተግባራትን እስካላሳዩ ድረስ በሕዝብና በሕዝብ ስም በሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች መካከል የላላ ግንኙነት ሊኖር ይችላል። በአንድ ሕዝብ ስምም እርስበርሳቸው የሚቃረኑና እንዲየውም የጨቋኙ ሥርዓት ወኪል ሆነው የሚያገለግሉ ድርጅቶች በአማራ፣ ኦሮሞ፣ ጋምቤላ፣ ወዘተ… የሕዝቡን አንድነትና ትግል አሰናክለዋል፡፡

የወረቀት ላይ ነብር በመሆን የአውራ ጎዳና መፈክሮችን እያነበነብን 25 ዓመታትን አሳልፈናል። ሆኖም እውነቱን እየተነጋገርን ከድክመቶቻችን በመማር አስተሳሰባችንን ብናርም የተሻለ ውጤት ልናገኝ እንችል ነበር። እውነቱ ከወያኔና የጥቅም ተካፋዮቻቸው ግለሰቦች በስተቀር የሥርዓቱን መለወጥ የማይፈልግ አለመኖሩ ነው። ቢሆንም ጉዳት ሊያደርስ በሚችል አውሬ ላይ መሰንዘር ሳይሆን በእርግጠኛነት መትቶ መጣል ካልተቻለ ተመልሶ በተጎነተለ አውሬ መጠቃትን እንደሚያስከትል ሁሉ፣ ስለወያኔ መወገድ ሲነሣ ማንም ኃላፊነት የሚሰማው ሰው እንደ የቆሰለ አውሬ ሆኖ እንዲቀር ሳይሆን፤ ሊያስወግደው የሚችለውን ሕዝባዊ መሠረት ማየት

ይፈልጋል፤ ሊተካው የሚችል ብቃት ያለውን አካል በኅሊናው መዳሰሱ ሐቅ ነው። የተሻለ እንጂ የባሰበትም እንዳይመጣ የፈልጋል። የፖሊቲካ ድርጅት ዓይነተኛ ሕዝባዊ ሚና መንግሥት ገልብጦ ሥልጣን እንዴት እንደሚገኝ ማቀድና መታገል ብቻ ሳይሆን፤ ሕዝቡ የሥልጣን ባለቤት መሆኑን አምኖ ሕዝቡ ለዚያ እንዲበቃ ለሕዝቡ ፍላጎት በመገዛት፣ ምጣኔ ሀብት አድጎ ሕዝቦች በልጽገው ማኅበራዊ እድገት ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ሰፍኖ ሕዝቦች ከሌሎች ሕዝቦች ጋር በእኩልነት፣ በፍቅር፣ በሰላም እና በደስታ መኖርን ስለሚፈልጉ፤ የዚህን ራዕይ የሚያመለክታቸውን ድርጅት ማየት ይፈልጋሉ። ጥላቻንና ልዩነትን የሚሰብኩ ድርጅቶች ግን አገር መምራት እንደማይችሉ ይርዳል።

አብርሃ ደስታ እንደገለጸው የፖሊቲካ ትምክህት የተጠናወታቸው ጥቂት ብሔርተኛ ድርጅቶች የየራሳቸውን ቡድን ከማየት በስተቀር የቀረው ብሔር-ብሔረሰብ አይታያቸውም፤ የሚያደርጉትም ትግል የተናጥል ነው፣ እነሱም ከምኞት ያለፈ አንዲት ስንዝር መራመድም አልቻሉም። ስለሆነም ሕዝቦች የወደፊቱን አገር እጣፈንታ ለማየት የሚያስችላቸው ራዕይ ከሌለ ምን አይተው በሕዝብ ስም የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶችን አቅፈው ነው የራሳቸው አካል የሚያደርጉት? ልዩነቶቻቸውን ይዘው ሰላማዊ ውይይት ለምሳሌ በዲያስፖራ እንኳ ሲያደርጉ አይታዩም፤ ገለልተኛ የሆኑ አካላት መድረክ አመቻችተውላቸው እንኳ ሊጠቀሙበት አልቻሉም፤ “የማያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል” እንዲሉ ስለዲሞክራሲና ፌዴራሊዝም እያነበነቡ፤ ዛሬ ከተቃዋሚዎቻቸው ጋር በጋራ የአገር ጉዳዮች ላይ በጋራ መስክ አንድነት ፈጥረው ለጋራ እርምጃ ያልተሰለፉ ድርጅቶች እንዴት አገርን የሚያኽል ትልቅ ነገር የመምራት ብቃት ይኖራቸዋል ብሎ ሕዝብ ሊተማመንባቸው ይችላል?

የድሮዎችንና የቅርብ ፖሊቲካ ፓርቲዎችን አነሳስ፣ አወዳደቅ ወይም ስኬታማነት የማይጠቃቅስ የፖሊቲካ ድርጅት የለም፤ ለምሳሌ በፈረንሳይ ሮቤስፓየር የመራቸው ጃኮቢኖች ቅጥ ያጣ ሥልጣን አብዮቱን ቀልብሶ ኋላ ያስከተለውን የናፖሊየን ቦናፓርት አምባገነናዊ አገዛዝ፣ በኮንጎ ፍትሐዊ በሆነ ምርጫ የተመረጠው ፓትሪስ ሉሙምባን ለመጣል የተፈጸመውን የኢምፔሪያሊስቶች ሴራ እና የነሙሴ ሾምቤ በውጭ ድጋፍ የመገንጠል ዓላማ ይዞ መነሣትና ከነዚህ ጋር ተያይዞ ከፍተኛ ምጣኔ ሀብት ያላት ኮንጎ ተከፋፍላ ወደኃላ መቅረት፣ በናይጄሪያ የነያኩቡ ጎዋንን አነሣስ፣ ውድቀትና የነኮሎኔል ኦዱሚኩ ኦጁኩ የመገንጠል ዓላማ ቢከሽፍም ከዚያ በኋላ

ተያይዘው የተከሰቱት ተከታታይ አምባገነናዊ መፈንቅለ-መንግሥቶች አገሪቷን ማዳከም፣ ጋናን ከአፍሪቃ አንድነትና ነፃነት /pan-African Movement/ ጋር ለማራመድ ራዕይ የነበረውን የቅዋሚ ንክሩማን በኢምፔሪያሊስቶች ሴራ መገልበጥ እና ሕዝባዊ ሕልሙን ማጨለም፤ በቺሊ በሕዝብ የተመረጠውን ሳልቫዶር አየንዴን መንግሥት በመገልበጥ በአውግስቶ ፒኖሼ አምባገነናዊ ሥርዓት እንዴትና ለማን ጥቅም እንደተተካ፣ በደቡብ አፍሪካ የነፒተር ቦታን የአፓርታይድ አገዛዝ በመቃወም እሥር ቤት እያለ አፍሪካን ናሽናል ኮንግሬስ የተባለውን የፖሊቲካ ድርጅት መሪ መሆኑ የሚታወቀው ጥቁሩ ኔልሰን ማንዴላ በድምፅ ተመርጦ ፍትሐዊነትን በማምጣት ለነጮቹም ትምህርት ሰጥቶ ሰላም መፍጠር፤ እንዲሁም የየመንን፣ የሶማሌን፣ የዩጎዝላቪያን ተከፋፍሎ በድህነት መቅረት፣ የርስበርስ መለያየት በኢራቅ፣ ሲሪያ ያስከተለው ጥፋት፣ ወዘተ… በተመሣሣይ ሁኔታ በአገራችን የሕዝቡን አብዮት ወደወታደራዊ አምባገነናዊ አመራር የለወጠው ደርግ በተለይም በኃይለሥላሴ አገዛዝ የተፈጠረውን የኤርትራን ጉዳይ ደርግም ሆነ ወያኔ ፍትሐዊ መፍትሔ ሊያስመጡ አለመቻላቸውና እንዲየውም ከነጉ የተነሣቸው ወያኔ ይህን ተጠቅማ ሕዝቡን በጎሣና በሃይማኖት ከፋፍላ በዚህ ክፍፍል ላይ ተንሠራፍታ በአምባገነንነት መቆየት፤ ወያኔን ለሥልጣን ያበቃውና አሁንም ማን እና ለምን እንደሚደግፋት የማያውቅ ወይም ማወቅ ያልነበረበት የፖሊቲካ ድርጅት ይኖራል ተብሎ አይታመንም። ስለ አገር ጉዳይ የተደራጀ አካል የአገራችንን ታሪክ ቢችል ከሞላ ጎደል የጥንቱን ከቅርቡ ጋር አገናዝቦ ለምሳሌ ከ 17 ኛው መቶ ክ/ዘመን ጀምሮ እስከ አሁን ያሉትን ታሪኮች እንኳ ጠንቅቆና ተረድቶ ከዓለም ዕድገቶች ጋር አገናዝቦ ቢያመዛዝን ለሕዝቦቻችን የሚጠቅመውን መረዳት አይሳነውም።

ታሪክን ወደኋላ የምናየው ካለፈው መልካም መልካሙን ለመውሰድና አሻሽሎ ለማዳበር ነው፣ በማወቅ ወይም ባለማወቅ የቀድሞ መሪዎች ባጠፉት ጥፋት ያሁኑን ትውልድ ለመበቀል ሳይሆን ካለፈው ስህተት ወይም ጥፋት ለመማርና ወደፊት እንዳይደገም ለማድረግ መሆን ይኖርበታል፤ እነ ቅዋሚ ንክሩማ፣ ኔልሰን ማንዴላም ሆኑ የነገሥታት እናት ተብለው የሚታወቁት የሖዲያ ተወላጅ ንግሥት እሌኒ፣ እነፍታውራሪ አባዶዮ ዋሚ፣ ጀ. ጃጋማ ኪሎ፣ ደጃዝማች ባልቻ አባነፍሶ፣ ራስ እምሩ ኃይለሥላሴ፣ ነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ፣ መኮንን ሀብተወልድ፣ ወዘተ… በቁጥር ሊወሰኑ የማይችሉ አያሌ አያቶቻችን አገር ለመገንባት አርቀው ወደፊት ያስተዋሉትን በመገንዘብ አገራችንን ለማሳደግና ሕዝቦቻችንን ለማበልፀግ ምን ማድረግ አለብን ብሎ ማሰብን ይጠይቃል። ነፃ አገር መሆን እንደብርቅ በሚታይበት ዘመን ሕዝቦቻችን ባደረጉት ትግል የኢትዮጵያን ነፃነት አስጠብቀው ስላቆዩዋት የአፍሪካ አንድነት ድርጅት መሥራች አገር መሆንዋና የተባበሩት መንግሥታት ቻርተርን ካረቀቁት አገሮች አንድዋ መሆንዋ በዓለም ኅብረተሰብ ዘንድ ከፍተኛ ቦታ የነበራት አገር መሆኗ ማንኛውንም ኢትዮጵያዊ ሊያኮራው ይገባል።

ዛሬ ግን በወያኔ አመራር ሕዝቦቻችን በጎጥና በጋጥ ደረጃ እንዲያስቡ እየተደረገ ሲሆን የፖሊቲካ ድርጅቶች በወያኔ ወጥመድ ውስጥ መዳኸር ሳይሆን ይህን በወያኔ የከፋፍሎ መግዣ መረብ ለመበጣጠስ አስፈላጊውን ሚና እንዲጫወቱ ይጠብቅባቸዋል። የኢትዮጵያን ሕዝቦች እንደቤተሰቡ የሚያይ አካል በአገራችን ታሪክ ኮርቶ፤ ተፈጽመው የነበሩ ስህቶቶች እንዳይደገሙ ወይም እንዲታረሙ ለተሻሻለ አስተዋፅዖ በሚደረግ ጥረት ቀዳሚ ሚናዎችን ለመጫወት ይሞክራል፤ ሕዝቡ ለጋራ ጥቅሞቹ እንዲተባበር ያደርጋል እንጂ ጥቋቁር የታሪክ ጠባሳዎችን እየፈለገ እንዲጋጭ አያደርግም።

በአገራችን መከፋፍል አያምንም፤ የከፋፋይ ወኪልም አይሆንም። መከፋፈል ኃይልን ማዳከም መሆኑን ለማረጋገጥ የባለሙያ ትንተና አያስፈልገውም፤ የሕዝቦች ኅብረት ወይም አንድነት ደግሞ የአገር ሉዐላዊነትን ለማስከበር ያስችላል፤ ይኸውም ዳርድንበርን ጠብቆ ብሔራዊ ባንዲራን በማውለብለብ ከማቆየት አልፎ፣ መሬትን፣ ወንዞችን፣ የባህር በሮቹን በሚያካትተው የአገሪቱ ምጣኔ ሀብት ላይ ውሳኔ የመስጠትና የመጠቀም የሕዝብ ኃይል ማምጣት ዋናው ነገር ሆኖ፤ በምጣኔ ሀብቱና በፖሊቲካው የተጠናከረ የሕዝብ ኃይል መፍጠር በቀጥታም ሆነ በእጅ አዙር ሊመጣ የሚችልን የውጭ ተፅዕኖ ማስቀረት ሲሆን፤ አገር ወዳድ ፖሊቲከኛ የሚቆመውም ለዚህ ዓይነት ሕዝባዊ ዓላማ ነው መሆን ያለበት፡፡

የአገራችን ትልቁ ታሪካዊ ችግር ኋላቀርነት ሲሆን ለዚህ አስተዋጽኦ ያደረጉት፣ በሥልጣን ሽኩቻ የአካባቢ የበላይ ለመሆን የተደረጉ የዘመናት የርስበርስ ጦርነቶች፣ ብሎም አምባገነን መሪዎች ሲሆኑ፣ በኋላቀርነታችን የሚጠቀሙ ቅኝ ገዥዎችና ኢምፔሪያሊስቶችም መሆናቸው መዘንጋት የለበትም። በአንድነታችን ሕዝቦቻችን ሁሉ የጥቅም ተካፋይ ሊሆኑ ሲችሉ፤ በልዩነታችን የሚጠቀሙት ሦስተኛ ወገኖች ናቸው፤ ለምሳሌ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር ብትቆይ ኖሮ ሌሎች ነገሮችን ትተን የባህር በሮቹ ለሁሉቱም ይጠቅሙ የነበረ ሲሆን፤ ዛሬ ግን ተጠቃሚዎቹ ኢምሬቶችና ሳኡዲዎች ሆነዋል። እንዲህ ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ እንዲያምቻቸው ነው ዛሬ ኢምፒሪያሊስቶች ያልበለፀጉ አገሮች ተከፋፍለው እንዲዳከሙ የሚያደርጉት፡- ለምሳሌ ኮንጎ፣ ኮሪያ፣ የመን፣ ዩጎዝላቪያ፣ ቼኮዝሎቫኪያ፤ ኢትዮጵያ ይገኙበታል። በአንፃሩ አንድነታቸውን በመጠበቃቸው ከተጠናከሩት ውስጥ ጀርመን፣ ቪየትናም፣ ቻይና፣ ካናዳ፣ ሕንድ፣ ብራዚል፣ ወዘተ…ን ይመለከቷል።

አገርን የመበታተን ድርጊቶች የሚፈጸሙት በነፃነት ስም ሲሆን፤ እንኳን ሕዝቡን በቋንቋው እየተናገሩ በነፃነት ስም

የሚከፋፍሉት ከሕዝቡ ውስጥ የወጡ ለሕዝቡ ቆመንለታል ባዮች መሆኑ ቀርቶ የውጭ ወራሪዎች እንኳ ሲወሩ ሕዝቡን “ብርሃንና ብልፅግና ይዘን መጣንላችሁ…” ማለታቸው ይታወቃል። ሕዝብ ግን ለተከታታይ ትውልድ ጭምር የሚጠቅመውንና የሚጎዳውን ለይቶ ያውቃል። የቅኝ ገዥዎች ቅኝ ግዛትን የጀመሩት ከአካባቢ የጎሣ መሪዎች ጋር ውለታ በሚፈጸሙ ወኪሎቻቸው አማካይነት እንደነበረ ሁሉ፤ በብሔርተኝነት የሚፈጠሩ አገሮች መሪዎችም ባለማወቅ ወይም አውቀው ለሥልጣን በመጓጓት ለጥቅም ናፋቂ የውጭ አገሮች በወኪልነት የሚያገለግሉ ሲሆን፣ የሚፈጠሩት ትናንሽ አገሮች ራሳቸውን ስለማይችሉ እርዳታ በመሻት የኃያላን አገሮችን ጥቅም ለማስጠበቅ የተመቹ ሆነዋል።

ኢትዮጵያ ሉዐላዊነቷን ጠብቃ ልትቆይ የቻለችው የተለያዩ የጥንት ወራሪዎችን በተለይም ፎይኒሺያውያን የሚባሉትን አይሁዶች፣ ሒምያሮችን፣ አረቦችን፣ አውሮፓውያንን፣ ወዘተ፣ በአንድነት የመከላከል ባህልና መልካም እሴቶች ስለአሉን። ከወረራ በመከላከል አገራቸውን በነፃነት ለማቆየት በተደረገው ጥረት ውስጥ ሕዝቦቻችን የተፈጥሮ መልከአምድሮችን ማለትም ተራሮችን፣ ባህሮችን እና ወንዞችን እንዲሁም በረሃዎችን ጭምር እንደመከላከያ በመጠቀም በተነፃፃሪነት ሲታይ ከሌላው ዓለም ጋር ግንኙነታቸው ውሱን ቢሆንም አገራችንን በነፃነት ሊያቆዩ ችለዋል፤ በእርስበርስ ግጭቶች፣ በወረራ፣ በወረርሽኝ በሽታና የተፈጥሮ መዛባት የተነሣ ብዙዎች ተሰደዋል፤ መቼና እንዴት እንደሆነ ለጊዜው ባይታወቅም በእንዲህ ያለ ነውጥ ከኢትዮጵያ ፈልሰው ወደአፍሪካ መኸል የተበተኑ የቱትሲ፣ የማሳይ ሕዝቦችን፣ ወደመካከለኛው ምሥራቅ የፈለሱትን የቤጃ/በደዊን ጎሣዎችን በምሳሌነት ማየት ይቻላል።

ኢትዮጵያውያን ጥቃቅን የውስጥ ልዩነቶች ይኖራቸው እንጂ በውስጥ ባሳለፉት ያንድነትና የግጭት አያሌ ዘመናት የእርስበርስ መስተጋብሮቻቸው ስለሚአይሉ ከሌላው ዓለም ሕዝቦች የተለዩ እንዲሆኑ አድርጎቸዋል፡- ዛሬ አማራ፣ ኦሮሞ፣ ከምባታ፣ ጉራጌ፣ ወዘተ… በማለት በብሔር-ብሔረሰቦች ለይተን የምናያቸው ሕዝቦቻችን በውስጣቸው እስከብዙ መቶዎች ከሚቆጠሩ ቀዳሚ ኅብረተሰቦች የተዋለዱና በዘር የተቀላቀሉ መሆኑን የባለሙያዎች ጥናት ያመለክታል። በተለያዩ ሰው-ሠራሽና ተፈጥሯዊ ክስተቶች የተነሣ የሕዝቦች ከአንዱ አካባቢ ወደሌላው መዘዋወር ወይም መሰደድ ሲፈጸም ኖሯል። በኢትዮጵያ ያሉ ብሔር-ብሔረሰቦች የስደት፣ የዝውውርና የመዋለድ ውጤቶች ናቸው፤ ለምሳሌ አማርኛ ከአረብኛ፣ ከአገውኛ፣ ከግዕዝ፣ እንዲሁም ሌሎች ቋንቋዎች ተከላልሶ በራሱ ነባራዊ ሁኔታ ተፈጥሮ ስላደገና የብዙ ሕዝቦች መግባቢያ ስለሆነ ነው ብሔራዊ ቋንቋ ሊሆን የቻለው፤ አማርኛ በ 10 ኛው መቶ ክፍለ-ዘመን በተነሣው የዛጉዌ (ኩሻዊ) ሥርወ-መንግሥት የዳበረ ቋንቋ እንደሆነ ይታወቃል።

እንዲሁም ከ 16 ኛው እስከ 19 ኛው ክ/ዘመን አጋማሽ ድረስ በተከናወነው የኦሮም ሕዝብ ፍልሰት የተነሣ አብዛኛዎቹ ሌሎች ኅብረተሰቦች ቋንቋቸውና ባህላቸው በኦሮሞ ተውጧል፡፡ ዛሬ አማርኛን ባእድ ያደረጉ የኦሮሞ ፖሊቲከኞች ለምሳሌ ኦሮሞዋ ንግሥተ-ነገሥታት ዘኢትዮጵያ ሕንደኬ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከኦሮሞ ወገን መሆንዋን እና ኦሮሞ ኢትዮጵያዊና የግዕዝ ቋንቋ ባለቤት መሆኑን፤ የኦሮሞ ነገሥታት ግዕዝ እየተናገሩ ከሰሜኑ ክፍለሀገራችን ኢትዮጵያን የገዙ መሆናቸውን ቢገነዘቡ፤ በቅርቡ እንኳ የኦሮሞ ሠራዊት በአድዋ ላይ ከሌሎች ኢትዮጵያኖች ጋር ደሙን አፍስሶ በፈጸመው ጀብዱ ይህችን አገር ካቆዩት ሕዝቦች መካከል በከፍተኛ ደረጃ የተሰለፈ መሆኑን፣ በማይጨው፣ በጨለንቆ እና ሶማሌያ ወረራ የጋራ አገራችንን ለመከላከል የፈጸመውን ተጋድሎ፤ ከጣልያን መሸነፍና ከኢትዮጵያ መውጣት በኋላ እንግሊዝ የግኝ ግዛት ምኞቷን ለመቀጠል ያደረገችውን ጥረት ለማምከን እነ ክቡር አቶ ይልማ ዴሬሳ ያደረጉትን ዲፕሎማሲያዊ ትግልና ድል ፤ ወዘተ ቢያውቁ ኖሮ ኦሮሞን ወያኔ በከለለው “ኦሮሚያ” ከመወሰን ይልቅ መላው ኢትዮጵያ አገራቸው መሆኑን ተረድተው አያቶቻቸው የገነቡት አገር እንዳይፈርስ ከሚቆሙት ውስጥ የመጀመሪያዎቹ ይሆኑ ነበር።

ኢትዮዮጵያን ኢትዮጵያ ያደረገው መሬቱ ብቻ ሳይሆን የሕዝቦቹ የዘመናት መዋሓድ ውጤት ነው፤ ኢትዮጵያውያን ተመሣሣይ የቆዳ ቀለም፣ ተመሣሣይ አመጋገብ፣ ተመሣሣይ አለባበስ፣ ተመሣሣይ የፀጉር አበጣጠር፣ ተመሣሣይ የሙዚቃ/ዘፈን ቅኝት፣ ተመሣሣይ እምነት፣ በአጠቃላይ ተመሣሣይ ባህል ሊኖራቸው ችሏል፤ አንድን ኢትዮጵያዊ በቆዳው ቀለም ብቻ ሳይሆን በአረማመዱ፣ በጥላውና በስሜቱ እንኳ መለየት ይቻላል። አማራ፣ ኦሮሞ፣ ትግሬ፣ ጉራጌ፣ ሲዳማ፣ ወላይታ፣ ወዘተ የሚሉት መለያዎች በተወሰነ የታሪክ ዘመን የተከሠቱ ነገሮች ሲሆኑ፣ ኢትዮጵያውያን ከዚያ የበለጠ ትሥሥር እና አንድነት የነበራቸው ሕዝቦች ናቸው። ሦስቱ ታላላቅ ሃይማኖቶች – የአይሁድ እምነት፣ ክርስትና እና እስልምና በብዙ የአውሮፓ፣ አፍሪቃ፣ አሚሪካና እስያ ክፍለ ዓለሞች ሁሉ በፊት ለመጀመሪያ ጊዜ የገቡት ወደ ኢትዮጵያ ነው። ኢትዮጵያ የስዎችን ሰብአዊ መብት በማክበር እና በልዩነት ተከባብሮ በመኖር በምሳሌነትዋ በቀዳማዊነት የምትታወቅ አገር እንደነበረች የንጉሥ አርማህ/ሙስሊሞች ነጃሽ ብለው መስጊድ በስሙ የሠሩለትን/ በ 7 ኛው መቶ ክ/ዘመን የነበረን የኢትዮጵያ መሪ በመረጃነት ማየት ይቻላል።

የአገራችንና የብዙ ሌሎች አገሮችን ታሪኮች ብናስተያይ በተለይ በ 18 ኛውና 19 ኛው እስከ 20 ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት በአንድ በኩል ትናንሽ የአካባቢ መንግሥታትን በውዴታም ሆነ በግዴታ አንድ አገር እንዲሆኑ በየክፍለዓለማቱ አገር

የማቅናት/unification/ ድርጊት ሲከሠት፣ ይህን ተከትሎ በተለይ አውሮጳውያን አገሮች የምጣኔ ሀብት ምንጭ /resource/ ለማግኛት ባደረጉት ሽምያ ደካማ አገሮችን በቅኝ የመያዝ ሂደት ውስጥ ሲያልፉ የያዙዋቸውን አገሮች ድንበር በመወሰንና በሕዝቦቹ ማንነት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አድርገውባቸዋል። የብዙ አፍሪካ አገሮች ካርታ በዚህ መሠረት የተፈጠረ ሲሆን በአፄ ምኒሊክ ዘመን በአንድ በኩል የውጭ ተስፋፊዎችን በመቋቋም በሌላ ብኩል አገርን ከውስጥ የማቅናት ተግባር ባይፈጸም ኖሮ የኢትዮጵያ ካርታ የተለየ ሊሆን ከመቻሉም በላይ ዛሬ የምናውቃቸው የአንዳንድ ብሔር-ብሔረሰቦች ማንነት /identity/ ሊጠፋ ወይም ሊለወጥ ይችል ነበር።

አገር በሚባለው ነገር ውስጥ ብዙ የተለያዩ የአመለካከት/የፍልስፍና፣ የጥቅም፣ ወዘተ ግጭቶች ይኖራሉ፤ እንኳን በአገር ውስጥ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ እንኳን ልዩነቶችና ግጭቶችም መኖራቸው የታወቀ ሲሆን፣ አገርን መምራት እነዚህን ልዩነቶችን አቻችሎ አገራዊ መፍትሔ በመስጠት ማስተናገድ ነው። ዛሬ በልፅገው የምናያቸው አገሮች ተመሣሣይ ችግሮች ሳይኖራቸው ቀርቶ ሳይሆን፤ በአገሮቻቸው ውስጥ የተለያዩ ሕዝቦች ተከባብረው በዲሞክራሲ ታቅፈው በመኖራቸው ነው ሊበለጽጉ የቻሉት። ሕዝብ በቀናነት የሚጠብቀው አገር ወዳድ ፖሊቲከኞች ልዩነቶችን ተከትለው እንዲከፋፍሉት፣ እንዲበታትኑት ሳይሆን በልዩነቶቻችን ላይ ዲሞክራሲ እንዲሰፍንና ጠንካራ የጋራ አገር ማድረግን ነው።

ሆኖም አንዳንድ ጠባብ ፖሊተከኞች እንደ መንጋ ሕዝብን ወደሚፈልጉት አቅጣጫ ለመንዳት መሞከራቸው ለአገር እድገት ሳይሆን ለሁሉም ድክመት ነው አስተዋፅዖ ያደረገውና የሚያደርገው። ስለሆነም ማንኛውም ሕዝብ ደጉንና ክፉዉን፤ ልማትና ሰላም የሚያመጣውን እና በአንፃሩ የተስፋ ዳቦ ብቻ የሚመግበውን ለይቶ የሚሰማበትና የሚያይበት ብዙ ጆሮዎችና ብዙ ዓይኖች ስለአሉት በሕዝባዊ መሠረታዊ ፍላጎቶችና ጥቅሞች ላይ ያልተማከለ የፖሊቲካ ድርጅት የሕዝቦችን ድጋፍ አግኝቶ ለአስተማማኝ ሕዝባዊ ድል መብቃት አይችልም። በአጠቃላይ ማንኛውም ሕዝብ ለማፍረስ ከመሰለፉ በፊት በሚፈርሰው ፋንታ ግንባታ ስለመኖሩ አሳማኝ ምልክቶችን በመሬት ላይ ማየት ይፈልጋል።

ሕዝቦችን ማዕከል ያደረገና አገርን የሚያማክል የጋራ ራእይ ያለው የፖሊቲካ ተቋማት ጥምረት ወይም ኅብረት ከሌለ ሕዝባዊ የጋራ ትግል ሊኖር አይችልም፤ ስለዚህ እስከአሁን ሕዝቡ ለጋራ ዓላማ ተሰልፎ ወደድል ያልተመራ መሆኑ ሊያስደንቀን አይገባም፤ ያልዘሩትን መሰብሰብ ስለማይቻል።

ማፍረስንማ ወያኔዎች ተክነውበታል፤ በመተማ፣ በአድዋ፣ በማይጨው፣ በጨለንቆ፣ ወዘተ ጦርነቶች በጋራ ተሰልፎ የጋራ አገር ያቆየውን ሕዝብ የታሪክን ደካማ ጎኖች /ጠባሳዎችን/ አጉልቶ በማቅረብና ሕዝቦችን በዘር አከፋፍለው በማካለል፤ በሃይማኖትና ቋንቋ በማናቆር እርስበርሱ የማያቃርጥ ግጭት ውስጥ እንዲገባ እና በአንፃሩ ለጋራ የአገር ጉዳይ እንዳያስብ አድርገውታል፤ የነፃነትንና የፍትሕን መርህ አዛብተው በበረቶች እንደሚለያዩ ከብቶች ሊነዱት ሞክረዋል፤ አሞሌ እየላሱ እረኛቸውን እንደሚከተሉ ሙክቶች የራሳቸውን ሕዝብ በጭቆና ለማስገዛት ወኪል የሆኑላቸው መሪዎችንና ቅጥረኞችንም/mercenaries/ ተጠቅመውባቸዋል፤ ለዘመናት አብሮ የኖሩትን ሕዝቦች ታሪክ በመቶ ዓመት ውስጥ ገድበው የጋራ አገር እንዳልነበራቸው አድርገው ታሪካቸውን አዛብተዋል።

በይህ መሠሪ ሴራቸው እስካሁን በሥልጣን ራሳቸውን ለማቆየት ተሳክቶላቸዋል። ሞኝ እስካለ ድረስ ሌባ የሚሠርቀው አያጣምና፤ በወቅቱ ስህተትን ማረም አዋቂነትና ጥንካሬ ሲሆን ከስህተት የማይማር ከመጃጃል ስለማያልፍ እንኳን መገንባት ማፍረስም አይሆንለትም። በእርግጥ ለሕዝብ የቆመ ከሆነ መገንባት እንደሚችል ያሳየ ድርጅት ለማፍረስ የሚተባበረው አያጣም።

ተፈራ ድንበሩ